የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፥ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፥ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሚያዚያ 10 2014

ቁጥር/REF NO: 02/247/628/14

ለሁሉም ዩኒቨርስቲዎች
**ባሉበት**

ጉዳዩ፡- **የትምህርት ፕሮግራሞች የቆይታ ጊዜን ይመለከታል**

በሀገራችን የትምህርት ሥርዓት የታዩ ክፍተቶችን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ለመስጠት እንዲቻል የፍኖተ ካርታ ጥናት ተካሂዶ ምክረ-ሃሳብ መቅረቡ ይታወሳል፡፡ በምክረ-ሃሳቡ መነሻነት በርካታ የለውጥ ሥራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡ ከነዚህ የለውጥ ሥራዎች መካከል በከፍተኛ ትምህርት እየተሰጡ ያሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች የጊዜ ቆይታን በተመለከተ የተተገበረው ምክረ-ሀሳብ አንዱ ነው፡፡ በዚህ መሠረት በከፍተኛ ትምህርት የሚሰጡ የመጀመሪያ ዲግሪ ፕሮግራሞች ከጊዜ ቆይታ አንፃር አራት ዓመት ሆኖ ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ተመላክቷል፡፡

| ተ.ቁ | የትምህርት ፕሮግራም/ባንድ | የቆይታ ጊዜ ማብራሪያ |
|---|---|---|
| 1. | ባንድ 1፡- (ኢንጂነሪንግና ቴክኖሎጂ የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር ከሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ ኮምፒውተር ሳይንስና አይቲ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ሲሆኑ የተቀሩት በሙሉ የአምስት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |
| 2. | ባንድ 2፡- (የተፈጥሮና ቀመር ሳይንስ የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች በሙሉ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |
| 3. | ባንድ 3፡- (የጤና እና ህክምና ሳይንስ የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር ከሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የህክምና እና የጥርስ ህክምና ዶክትሬት ዲግሪዎች የስድስት ዓመት፣ የፋርማሲ ትምህርት ፕሮግራም የአምስት ዓመት ሲሆን የተቀሩት የትምህርት ፕሮግራሞች በሙሉ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |
| 4. | ባንድ 4፡- (የግብርና እና ተፈጥሮ ሃብት የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር ከሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የእንስሳት ህክምና ዶክትሬት ዲግሪ በስድስት ዓመት የሚሰጥ ሲሆን የተቀሩት የትምህርት ፕሮግራሞች በሙሉ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Education

| | | |
|---|---|---|
| 5. | ባንድ 5፡- (የቢዝነስና ኢኮኖሚክስ የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር የሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች በሙሉ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |
| 6. | ባንድ 6፡- (የማህበራዊ ሳይንስ የትምህርት ፕሮግራሞች) | በዚህ ባንድ ሥር ከሚሰጡ የትምህርት ፕሮግራሞች ውስጥ የህግ ትምህርት የአምሥት ዓመት ፕሮግራም ሲሆን ቀሪዎቹ በሙሉ የአራት ዓመት ፕሮግራሞች ናቸው፡፡ |

ስለሆነም ከላይ በሠንጠረዡ በተቀመጠው የጊዜ እርዝማኔ መሠረት የኮርስ ካታሎግ እና ሥርዓተ ትምህርቱ ተጣጥሞ በየተቋማቱ አመራር የቅርብ ክትትል እየተደረገበት ሥራ ላይ እንዲውል አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፡-

- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ገንዘብ ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ፕላንና ልማት ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ግብርና ሚኒስቴር
- ለኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጤና ሚኒስቴር

  <u>አዲስ አበባ</u>
- ለከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት
- ለአካዳሚክ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ጀነራል
- ለፕሮግራሞችና ሥርዓተ ትምህርት ዳይሬክቶሬት

  **<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>**